የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በምርጫ ወቅት የኮቪድ- 19 ስርጭትን ለመቀነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር----9/2013

## ምዕራፍ አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀፅ 1. አውጪው ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 163 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

**አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ***"በምርጫ ወቅት የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/2013"*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 3. ትርጓሜ**

1. በዚህ መመሪያ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር **"ኮቪድ-19"** ማለት በዓለም የጤና ድርጅት ይህ ይፋዊ ስያሜ የተሰጠው ተላላፊ በሽታ ነው።
2. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።
3. **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
4. **"አካላዊ ርቀት"** ማለት በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይም ሁለት ሜትር ርቀትን መጠበቅ ነው ።
5. **"ስብሰባ"** ማለት ከምርጫ ጋር ግንኙነት ላላቸው እንቅስቃሴዎች ዓላማ የአንድ ቤተሰብ አባላት ያልሆኑ አራት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች በአካል ተገኝተው የሚያደርጉት መሰባሰብ ነው።

6. **"ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንቅስቃሴዎች"** ማለት የመራጮች ምዝገባን፣ የመራጮች ትምህርትን፣ የምርጫ ሠራተኞች፣ የእጩ ወኪሎች፣ የታዛቢዎች ወይም ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት ስልጠናን፣ የእጩዎች ምዝገባን፣ የእጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባዎችን፣ ቅስቀሳዎችን እና የድጋፍ ስብሰባዎችን፣ ድምፅ አሰጣጥን፣ የድምጽ ቆጠራን፣ በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች አፈታትን፣ ምርጫ መታዘብን፣ በምርጫ ዙሪያ በመገናኛ ብዙሀን የሚሰሩ ዘገባዎችን፣ የምርጫ ቁሳቁሶች ስርጭትና ማጓጓዝን እና ሌሎች የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል።
7. **"ፀረ ተዋህሲያን ማስወገጃ"** ማለት ዕቃዎችን ወይም በታዎችን ከተዋህሲያን ነጻ በማድረግ የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመቀነስ የሚያገለግል ቢያንስ 60 በሙቶ የአልኮል ይዘት ያለው ከአልኮል ወይም ከክሎሪን የተሰራ ውህድ ነው።
8. **"የኮቪድ-19 የምርጫ ግብረ-ኃይል"** ማለት በፌዴራል፣ በክልል እና በምርጫ ክልል ደረጃ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ተወካዮችን ያካተተ ግብረ-ኃይል ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንቅስቃሴዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በግብረ-ኃይሉ ውስጥ በታዛቢነት ሊሳተፉ ይችላሉ።
9. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት መሰረት የተቋቋሙት ክልሎች ሲሆኑ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል።
10. **"ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች"** ማለት ዕድሜያቸው 60 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ፣ ነፍሰጡር ሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች ናቸው። ትርጓሜው የአስም፥ የስኳር ወይም ከፍተኛ የደም ግፊት በሽታ እንዳለባቸው በግልጽ የሚያስታውቁ ወይም የሀኪም ማስረጃ ያላቸው ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ዝቅተኛ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸውንም ግለሰቦች ያካትታል።
11. **"የቦርድ ሠራተኛ"** ማለት በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ ውል መሠረት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተቀጠረ ሰው ነው።
12. **"የምርጫ ፀጥታ አስከባሪ"** ማለት ከምርጫ ጋር ግንኙነት ላለው እንቅስቃሴ ፀጥታ እንዲያስከብር ኃላፊነት የተሰጠው የፀጥታ አስከባሪ አካላት አባል ነው።
13. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት ሙብት የተሰጠው ሰው ነው።

14. በአዋጁ እና በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 ውስጥ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደአግባብነታቸው በዚህ መመሪያ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ምርጫ፣ በአካባቢ ምርጫ፣ በድጋሚ ምርጫ፣ በሟሟያ ምርጫ፣ በህዝበ ውሳኔ፣ በቦርዱ እና በቦርዱ በየደረጃው በተቋቋሙ አደረጃጀቶች እንዲሁም ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንቅስቃሴዎችን በሚመሩ እና በእንቅስቃሴዎቹ ውስጥ በሚሳተፉ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 5. የጾታ አገላጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተገለጸው ሌላኛውንም ፆታ ይመለከታል።

**አንቀጽ 6. ዓላማ**

የመመሪያው ዓላማ በምርጫ ወቅት ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንቅስቃሴዎች ሲከናወኑ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>የኮቪድ-19 ስርጭት የመቀነስ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት</u>

**አንቀፅ 7. የቦርዱ እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ኃላፊነት**

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ ጣቢያዎች እንዲሁም በየደረጃው ባሉ የቦርዱ ጽ/ቤቶች ከምርጫ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች ሁሉ አካላዊ ርቀት በጠበቀ ሁኔታ መከናወናቸውን ያረጋግጣሉ።
2. ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች በሚያከናወንበት ወቅት ማናቸውንም አካላዊ ንክኪዎች ማድረግ የለበትም።
3. የመራጮች ምዝገባ ወይም ድምጽ አሰጣጥ በሚከናወንበት ሂደት በምርጫ ጣቢያ ውስጥ አስፈላጊውን አካላዊ ርቀት ለመጠበቅ የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር የጣቢያው ኃላፊ ዕውቅና በተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች፣ በእጩ ወይም በፓርቲ ወኪሎች እና በጋዜጠኞች ቁጥር ላይ

በማንኛውም ጊዜ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል። የቁጥር ገደብ በሚቀመጥበት ጊዜ ሚዛናዊ የሆነና በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አስፈላጊው ግምገማ የሚደረግበት በተራ የመግባት ሥርዓት ተግባራዊ መደረግ አለበት።

4. በንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመለከተው የቁጥር ገደብ ውሳኔው እና የተራ መግባት ስርዓቱ ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ ተፈፃሚ መደረግ ይኖርበታል። የቁጥር ገደብ ውሳኔ አሰጣጥ ብሎም የተራ መግባት ስርዓቱ እንደአግባብነቱ በምርጫ ክልል ምርጫ አስፈፃሚዎች ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል።

    ሀ) በርካታ የእጩ ወኪሎች፣ እውቅና የተሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን እና ታዛቢዎች በአንድ ምርጫ ጣቢያ በሚገኙበት ጊዜ ተራቸው ሁሉም በተገኙበት በሚወጣ እጣ የሚወሰን ይሆናል፡፡

    ለ) የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የተራ መግባት ስርዓቱ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ታዛቢ በምርጫ ጣቢያው እንዳይገኝ የማያደርግ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል

5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው በመራጭነት ለመመዝገብ ለሚመጡ ሰዎች የቦርዱ የሰራተኞች መመሪያ የሚጠይቃቸውንና ሌሎች ማናቸውም የግል ንፅህና መጠበቂያ መገልገያዎች በመጠቀም የምርጫ ሰራተኞች ድጋፍ እንዳይሰጡ የሚከለክል አይሆንም።

6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የቤተሰብ አባላት እና ሌሎች ግለሰቦች አካላዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች አካላዊ ድጋፍ እንዳያደርጉ የሚከለክል አይደለም። ይሁን እንጂ አካላዊ ድጋፍ ሰጪዎቹ አስፈላጊ የሚባሉ ቅድመ ጥንቃቄዎችን በተለይም የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግ፣ ድጋፍ ከመስጠታቸው በፊት እና በኋላ እጃቸውን በሳኒታይዘር ወይም በውሃ እና ሳሙና ማጽዳት አለባቸው።

7. ቦርዱ አንድ ሰው መምረጡን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውለውን የማይለቅ ቀለም እና ቀለሙ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ በሚመርጥበት ጊዜ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ የሚያግዙ እርምጃዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

8. ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ጨቅላ ሕፃናትን ይዘው የሚመጡ ሴት የምርጫ አስፈፃሚ፣ የእጩ ወኪሎች፣ታዛቢዎችና ሌሎች ሰራተኞችን በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ።
9. የምርጫ ጣቢያዎች እና የምርጫ ክልል የምርጫ ጽ/ቤቶች፣ መራጮች፣ እጩዎች እና ሌሎች ባለጉዳዮች አስፈላጊውን አካላዊ ርቀት እንዲጠብቁ የሚያስችሉ ምልክቶችን እና መልዕክቶችን ስራቸውን በሚያከናውኑባቸው ክፍሎች፣ በቅጥር ግቢ ውስጥ እና ከቅጥር ግቢ ውጭ መለጠፋቸውን ያረጋግጣል።
10. የመራጮች እንቅስቃሴ ፍሰት በአንድ አቅጣጫ መሆኑን እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎች እና የምርጫ ክልል የምርጫ ጽ/ቤቶች በቂ የአየር ዝውውር እና የተለያየ መግቢያ እና መውጫ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል። መግቢያ እና መውጫ የመወሰን ሂደት የምርጫ ክልል ፅ/ቤቱን እና ጣቢያውን ለአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።
11. ቦርዱ ከጤና ሚኒስቴር አካላዊ ርቀት መመሪዎች ጋር የሚጣጣም አካልጉዳተኞችንና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረገ መረጃ ሰጪ ሞዴል የምርጫ ጣቢያ እና የምርጫ ክልል ምርጫ ጽ/ቤት አቀማመጥ ያዘጋጃል። ይህም ለምርጫ ጣቢያዎች እና ለምርጫ ክልል የምርጫ ጽ/ቤቶች የሚሆኑ ቦታዎች እንዴት መመረጥ እንዳለባቸው እና ምን ያህል ምርጫ ጣቢያዎች እንደሚያስፈልጉ መረጃ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል። ቦርዱ መረጃው የሠራተኞች ስልጠና መርሀ ግብሮች ላይ መካተቱን ያረጋግጣል።
12. የአካላዊ ርቀት እርምጃዎችን የማክበር አስፈላጊነትን ለህዝቡ እንዲሁም ከምርጫ ጋር ግንኙነት ባላቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች በሙሉ ያሳውቃል።
13. የምርጫ አስፈጻሚዎች በምርጫ ጣቢያዎች እንዲሁም በየደረጃው ባሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤቶች ውስጥ የመራጮች ምዝገባና የድምፅ መስጫ እለት አካላዊ ርቀት መጠበቁን መከታተላቸውን እና ማስፈፀማቸው ያረጋግጣል። አካላዊ ርቀት መከበሩን ለማረጋገጥ የምርጫ ጸጥታ አስከባሪዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ።
14. ቦርዱ ማንኛውም ከምርጫ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውን ሰው አካላዊ ርቀት መጠበቁን የማረጋገጥ ሀላፊነቱን ተግባራዊ ማድረጉን ይቆጣጠራል። ለዚሁ አላማ በቅጥር ግቢ ውስጥ እና ከቅጥር ግቢ ውጭ ምልክቶችን ማድረግ፣ ቅጥር ግቢውን የሚጠቀሙ ወይም

ዝግጅቶችን የሚታደሙ ሰዎች በሙሉ አንድ አቅጣጫ ባለው ፍሰት መንቀሳቀሳቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ፣ በተቻለ መጠን ዝግጅቶቹን ሁልጊዜ ከመሰብሰቢያ አዳራሾች ውጭ ወይም በቂ የአየር ዝውውር ባላቸው ቦታዎች መከናወናቸውን እንዲሁም በሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የአካላዊ ርቀት መስፈርቶች መከበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

15. የቦርዱ ሠራተኞች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ በምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎች፣ የምርጫ ታዛቢዎች፣ የፓርቲ ወይም የእጩ ወኪሎች፣ ዕውቅና የተሰጣቸው የመራጮች ትምህርት ሰጪዎች፣ ዕውቅና የተሰጣቸው ጋዜጠኞች፣ ከምርጫ ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ስልጠና የሚሰጡ እና በስልጠና ላይ የሚካፈሉ ሰዎች እና የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች በሙሉ ከምርጫ ጋር ግንኙነት ባላቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው።
16. በሁሉም የቦርዱ ቅጥር ግቢዎች እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎች መግቢያ ላይ የእጅ ሳኒታይዘር ወይም የእጅ መታጠቢያዎች (በቂ ውሃና ሳሙናን ጨምሮ) መኖራቸውን ያረጋግጣል። ወደ እነዚህ ቅጥር ግቢዎች ወይም የምርጫ ጣቢያዎች የሚመጣ ሰው ሁሉ ወደ ውስጥ ከመግባቱ በፊት እጆቹን በሳኒታይዘር የማፅዳት ወይም የመታጠብ ግዴታውን እንዲወጣ ያደርጋል።
17. በሁሉም የቦርዱ ቅጥር ግቢዎችእንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎች የኮቪድ 19 ስርጭትን በመቀነስ ረገድ አግባብነት ያለው የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፡፡
18. ከምርጫ አፈፃፀም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላላቸው ሠራተኞቹ በሙሉ እንደ አፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ያሉና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግል ደህንነት መጠበቂያ መገልገያዎችን ያቀርባል።
19. በሁሉም የቦርዱ ቅጥር ግቢዎች እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎች በኮቪድ-19 ስርጭት መቀነሻ እርምጃዎች ዙሪያ ይፋዊ መረጃ መሰጠቱን ያረጋግጣል።
20. ከቦርዱ ውጭ እያንዳንዱ ከምርጫ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውን ሰው የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን መጠቀሙን፣ በዚህ መመሪያ ላይ የተመለከቱት እጅን በሳኒታይዘር ማፅዳት ወይም በውሃና በሳሙና መታጠብ ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን ማክበሩን

እንዲሁም በቅጥር ግቢው ውስጥ ከኮቪድ-19 ስርጭት መቀነሻ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ ይፋዊ መረጃዎችን ለህዝብ የመስጠት ግዴታ መከበሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

21. በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (1) እስከ (20) ያሉ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ በሚከተሉት ሁኔታች እና ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም

    ሀ) በህክምና የተረጋገጠ የአተነፋፈስ ወይም ተያያዥ የጤና ችግር ባለባቸው ግለሰቦች እና

    ለ) ማንነታቸውን ለማረጋገጥ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብላቸውን እንዲያወልቁ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠራተኞች በሚጠየቁበት ጊዜ፣

    ሐ) በስብሰባዎች ላይ ለመናገር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብላቸውን እንዲያወልቁ የሚገደዱ ከሆነ፣

    መ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ለ እና ሐ ስር በተደነገገው መሰረት የአፍ እና አፍንጫ ጭምብላቸውን ሲያወልቁ አካላዊ መራራቅን የመሰሰሉ የኮቪድ-19 ቅድመ ጥንቃቄዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

## አንቀፅ 8. በምርጫ ወቅት የኮቪድ-19 የሥነ-ምግባር ደንብ ስለማውጣት

1. ቦርዱ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከጤናው ዘርፍ አካላት እና ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በምርጫ ወቅት በተለይም ለሴቶችና ልዩ ፍላጎት ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን አፅንኦት የሰጠ የኮቪድ-19 ሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጃል።
2. የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩዎች እንዲሁም ለመራጮች ትምህርት እንዲሰጡ፣ ምርጫውን እንዲታዘቡ ወይም እንዲዘግቡ ፈቃድ የተሰጣቸው ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንቡን ይፈርማሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

## <u>በምርጫ ሂደቶች የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመቀነስ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ዕርምጃዎች</u>

### አንቀፅ 9. የመራጮች ትምህርት

1. ፈቃድ የተሰጣቸው የመራጮች ትምህርት ሰጪዎች በዋነኛነት በመደበኛ እና በበይነ መረብ መገናኛ ብዙሀን አማካኝነት የመራጮች ትምህርት እንዲሰጡ ይበረታታሉ።
2. ትምህርቱን በአካል የሚሰጡ ከሆነ ክፍት ቦታዎችን እና በቂ የአየር ዝውውር ያላቸው ቦታዎችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።
3. የመራጮች ትምህርት መርሀ-ግብሮች ለኮቪድ-19 ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ የተለየ ሠዓት ስለመመደቡ እንዲሁም መራጮች የራሳቸውን እስክሪብቶ ይዘው ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዲመጡ ማበረታታትን ጨምሮ የኮቪድ-19ን መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች እና በምርጫ እንቅስቃሴዎች ወቅት ሊተገበሩ የሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማካተት አለበት፡፡
4. ለመራጮች ትምህርት እንዲሰጡ ዕውቅና የተሰጣቸው አካላት የሚያሰማሯቸው አሰልጣኞችና እና ተሳታፊዎች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ መጠቀማቸውን እንዲሁም በዚህ መመሪያ እና በሥነ-ምግባር ደንቡ ውስጥ የተቀመጡ የስርጭት የመቀነሻ መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
5. እውቅና በተሰጣቸው አካላት ትምህርቱን ለሁሉም ሰዎች ተደራሽ የማድረግ ጥረት ሴቶችና ሌሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በሚኖሩበት ወይም በሚሰሩበት አካባቢዎች እንዲሁም በየተደራጁባቸው መደበኛና ኢ-መደበኛ ማህበራትን በመጠቀም ማሰራጨትን ያካተተ መሆን ይገባዋል።

### አንቀፅ 10. የመራጮች ምዝገባ

1. ቦርዱ በመራጮች ምዝገባ ወቅት በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እና ውጪ አካላዊ ርቀት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ምርጫ አስፈጻሚ ወይም ሰልፍ አስከባሪ ይመድባል።

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እንደ እስክሪብቶ ያሉ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና የሚነካኩ ቁሶችን በየጊዜው በጸረ ተዋህሲያን ውህድ ወይም በአልኮል በተሰራ ሳኒታይዘር መጸዳታቸውን ያረጋግጣል።
3. ቦርዱ ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በምርጫው እለት የሚመዘገቡባቸው የተለዩ ጊዜዎችን ሊመድብ ይችላል። ይህንኑ ውሳኔ የመስጠት ሂደት ከኮቪድ 19 ጋር በተያያዘ የጤና ዕክል ምክንያት የቤተሰብ አባላትን በመንከባከብ ላይ የሚገኙ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን፣ አቅመ ደካሞችን፣ ጨቅላ ህፃናት ያላቸው ሴቶችን እንዲሁም ሌሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ከግምት ማስገባት ይኖርበታል።
4. ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ስር ከተመደቡት ጊዜዎች ውጭ ለሚመዘገቡ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች የሚያገለግል ልዩ የቅድሚያ መስተንግዶ መስመር ይመድባሉ።

## አንቀፅ 11. በእጩዎች የሚከናወን የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ

እጩ ተወዳዳሪዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች

1. ለእጩነት የድጋፍ ፊርማዎችን በሚያሰባስቡበት ወቅት የአካላዊ ርቀት መመሪያዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣
2. የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ መጠቀም እንዲሁም የፊርማ ማሰባሰብ ሂደቱን የሚያግዙ ግለሰቦች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ እና
3. እንደ እስክሪብቶ ያሉ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎች በየጊዜው በጸረ ተዋህሲያን ውህድ ወይም በአልኮል በተሰራ ሳኒታይዘር መጸዳታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

## አንቀፅ 12. ህዝባዊ ስብሰባዎች እና ቅስቀሳዎች

1. ከምርጫ ጋር በተያያዙ ስብሰባዎች እና ቅስቀሳዎች ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ መጠቀም አለባቸው።

2. የፖለቲካ ፓርቲዎች በስብሰባዎች እና በቅስቀሳዎች ወቅት የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመቀነስ የሚያግዙ እርምጃዎችን በሚመለከት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር አለባቸው።

3. በአዋጁ አንቀጽ 46(1) ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ በሚከተሉት ቦታዎች የምርጫ ቅስቀሳ ማከናወን የተከለከለ ነው፣

ሀ) በመንግስት ጤና ተቋማት፣

ለ) የኮቪድ 19 ህክምና እና ለይቶ ማቆያ ማዕከሎች፣

ለ) የአረጋዊያን ማቆያ ማዕከሎች።

## አንቀፅ 13. ስብሰባዎችን እና ቅስቀሳዎችን የማሳወቅ ግዴታ

1. ከ50 ሰዎች በላይ የሚሳተፉባቸው ከምርጫ ጋር የተያያዙ ስብሰባዎችን፣ የመራጮች ትምህርትን፣ ስልጠናዎችን እና የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን የሚያዘጋጁ አካላት ከሁነቱ ቢያንስ 48 ሠዓታት አስቀድመው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም አግባብ ላለው በክልል ወይም በምርጫ ክልል ደረጃ ላለ ጽ/ቤት በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።
2. **የኮቪድ-19 የምርጫ ግብረ-ኃይሉ** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ለተመለከተው ማሳወቂያ የሚያገለግል የማሳወቂያ ቅጽ እንዲሁም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች የያዘ ፕሮቶኮል እና የማረጋገጫ ዝርዝር ያዘጋጃል፤ ይህንንም ዝርዝር የተጠቀሱትን እንቅስቃሴዎች የሚያዘጋጁ አካላት በነፃ እና በቀላሉ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
3. ከምርጫ ጋር የተያያዙ ስብሰባዎችን፣ የመራጮች ትምህርትን፣ ስልጠናዎችን እና የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ለመከልከል የሚያበቃ ከፍተኛ የኮቪድ-19 ስርጭት ስጋት ያለ እንደሆነ በየደረጃው የሚገኝ የቦርዱ ፅ/ቤት ማሳወቂያው በደረሰው በ24 ሠዓታት ውስጥ ምክንያቶቹን በግልጽ በመጥቀስ ውሳኔውን በጽሁፍ ለአዘጋጁ አካል ያሳውቃል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር በተሰጠው የክልከላ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በየደረጃው ለሚገኝ የቦርዱ ፅ/ቤት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤ ፅ/ቤቱም አቤቱታው በደረሰው በ48 ሠዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

## አንቀፅ 14. ስለ ድምፅ መስጠት

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በምርጫው ዕለት በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እና ውጪ አካላዊ ርቀት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ምርጫ አስፈጻሚ ወይም ሰልፍ አስከባሪ ይመድባል።
2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እንደ እስክሪብቶ ያሉ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና የሚነካኩ ቁሶችና ገጽታዎች በየጊዜው በጸረ ተዋህሲያን ውህድ ወይም በአልኮል በተሰራ ሳኒታይዘር መፀዳታቸውን ያረጋግጣል።
3. ቦርዱ ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በምርጫው እለት የሚመርጡባቸው የተለዩ ሰዓቶች ሊመድብ ይችላል።
4. ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ከተመደቡት ጊዜዎች ውጭ ለሚመርጡ ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችየሚያገለግል ልዩ የቅድሚያ መስተንግዶ መስመር ይመድባሉ።

## አንቀፅ 15. የድምጽ ቆጠራ

ምርጫ አስፈጻሚዎች በድምጽ መደመር እና ቆጠራ ወቅት ጓንቶችን ማድረግ ወይም እጃቸውን እና በቆጠራ ወቅት በተደጋጋሚ የሚነካኩ ቁሳቁሶችን በየጊዜው በሳኒታይዘር ማጽዳትአለባቸው።

## አንቀፅ 16. ምርጫ ስለመታዘብ እና ስለመዘገብ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በተራ የመግባት ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የምርጫ ታዛቢዎች እና ዘጋቢዎች ከምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ጋር ተባብረው መሥራት አለባቸው።
2. የምርጫ ጣቢያ ሀላፊዎች ታዛቢዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማክበር የሚያስችላቸውን ግንዛቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ።

**አንቀፅ 17. የመራጮች መዝገብ እና የድምጽ ቆጠራ ይፋ ማድረግ**

1. በርዱ የመራጮች መዝገብ እና የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለህዝብ ይፋ በሚደረግበት ወቅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገጉት የኮቪድ 19 ስርጭት መቀነሻ እርምጃዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል።
2. በርዱ የመራጮች መዝገብ እና የድምፅ ቆጠራ ውጤት በተቻለ መጠን በመገናኛ ብዙኃን (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣና በመሳሰሉት) እንዲተላለፍ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል።

**አንቀፅ 18. በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሂደት**

1. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የቅሬታ መስሚያ ቦታዎችን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ ቁጥር 10 ላይ በተመለከተው በቦርዱ ሞዴል የምርጫ ጣቢያና የምርጫ ክልል ፅ/ቤት አቀማመጥ እና በጤና ዘርፍ በወጡ የአካላዊ ርቀት መመሪዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ።
2. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በተቻለ መጠን ጉዳዮችን ክፍት በሆኑ እና በቂ የአየር ዝውውር ባላቸው በታዎች ይሰማሉ።
3. ለሁሉም ባለጉዳዮች የእጅ ሳኒታይዘሮችን እና የእጅ መታጠቢያዎችን ከበቂ ውሃና ሳሙና ጋር ያቀርባሉ።
4. ወደ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚመጡ ባለጉዳዮች ሁሉ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ ማድረጋቸውን ያረጋግጣሉ።
5. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ጉዳይ በሚሰማበት ቦታ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ቁጥር በተመለከተ ገደቦችን ሊያስቀምጡ ይችላሉ።

## ምዕራፍ አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀፅ 19. የኮቪድ 19 የምርጫ ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም**

1. ቦርዱ በክልል ቅርጫፍ ጽ/ቤት፣ ምርጫ ክልል እና ምርጫ ጣቢያ ደረጃ የኮቪድ-19 የምርጫ ግብረ-ኃይል ያቋቁማል። ይህ ግብረ-ኃይል እንደአግባብነቱ ጤና ሚኒስቴር እና የክልል/ዞን/ወረዳ/ቀበሌ ጤና ቢሮዎችን ያካተተ ይሆናል፤ እንዳስፈላጊነቱም የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሊጋብዝ ይችላል።

2. በማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ ወቅት የኮቪድ-19 ምልክቶች የሚታይበት ግለሰብ ሲገኝ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ ግብረ-ኃይሉ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## አንቀፅ 20. ቅጣቶች

1. ይህ መመሪያ በሚጠይቀው መሰረት የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን ወይም አፍ እና አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛን ለመጠቀም እምቢተኛ የሆኑ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የቦርዱ ሠራተኞች፣ እጩዎች፣ ዕውቅና የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች፣ የፓርቲ ወይም የእጩ ወኪሎች እና ጋዜጠኞች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች፣ የቦርዱ ቅጥር ግቢዎች እና ቅሬታ መስሚያ ቦታዎች እንዳይገቡ ይደረጋሉ።
2. በምርጫ አስፈጻሚዎች አንድ መራጭ መምረጡን የሚያረጋግጥ የማይለቅ ቀለም ለመቀባት ፈቃደኛ ያልሆኑ መራጮች እንዲመርጡ አይፈቀድላቸውም።
3. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መጣስ አግባብ ባላቸው የጤና አጠባበቅን የሚመለከቱ እና የወንጀል ሕጎች መሠረት ሊያስቀጣ ይችላል።
4. ቦርዱ ስብሰባዎችን እና ቅስቀሳዎችን በተመለከተ የተቀመጡ ግዴታዎች ሳይከበሩ ስለመቅረታቸው ተጨባጭ መረጃ በሚደርሰው በማንኛውም ጊዜ መረጃውን አግባብ ላላቸው ሕግ አስከባሪ አካላት ያስተላልፋል።

## አንቀፅ 21. ስለ ልዩ እርምጃዎች

ቦርዱ አግባብነት ያላቸው የጤና አካላት ለይተው በሚያስቀምጡት የስጋት ደረጃ መሰረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚተገበሩ ድንጋጌዎችን ሊያስቀምጥ ይችላል። ይህም አንድ የተለየ መልክአ-ምድራዊ አካባቢን በተመለከተ ተጨማሪ መስፈርቶችን ማስቀመጥን ወይም በዚህ መመሪያ ውስጥ ለተቀመጡት መመሪያዎች ልዩ ሁኔታዎችን መፍጠርን ሊያካትት ይችላል።

## አንቀፅ 22 . መመሪያው በየጊዜው ስለማሻሻል

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች አፈፃፀም በሚገመግምበት ወቅት አግባብነት ያላቸው የጤናው ዘርፍ፣ በዚህ መመሪያ መሰረት የተቋቋመውን ግብረ-ኃይል፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላትን ያማክራል።

2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመዋጋት በሚወሰዱ የህብረተሰብ ጤና እርምጃዎች ላይ የሚደረጉ ለውጦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ዝርዝር የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓቶችን እና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**አንቀፅ 23. መመሪያው የሚፀናበት ቀን**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከየካቲት 4 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**ብርቱካን ሚደቅሳ**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**